# Lasix Renal Scan (ለይዚክስ የኩላሊት ምርመራ)



## ለይዚክስ የኩላሊት ስካን ምንድን ነው?

ለይዚክስ የሚባል የኩላሊት ስካን የልጅዎ ኩላሊት ምን ያህል እንደሚሰራ እና ኩላሊትን፣ ማህጸንን፣ እና ፊኛን (የሽንት ስርዓትን) የሚዘጋ ነገር ካለ የሚያሳይ ምርመራ ነው። ምርመራው MAG-3 ሬኖግራም ተብሎም ይጠራል። ትንሽ መጠን ያለው የሚከታተል ጠቋሚ (ራዲዮፋርማሱቲካል) ወደ ልጅዎ የደም ስር ቧንቧዎች እናስገባለን። ጠቋሚው በልጅዎ አካል ውስጥ ገብቶ እንዳለ፡ የሽንት ስርዓቱን ፎቶ እናነሳለን። ስካን ከተደረገ በኋላ የቀኝ እና የግራ የኩላሊቶች ክፍል ውስጥ ያለውን የኩላሊቱን ስራ መጠን ለማነጻጸር መለኪያ እናደርጋለን።

## ልጄን ስካን እንዲደረግለት እንዴት ማዘጋጀት እችላለሁ?

ወደ ሆስፒታል ከመምጣትዎ በፊት በምርመራው ጊዜ ምን እንደሚሆን ለልጅዎ ያስረዱ።

ልጅዎ ሕጻን ከሆነ፡ ስካን ከተደረገ በኋላ እንዲሰጡት፡ አንድ የፎርሙላ ወተት ወይም ጭማቂ ይዘው መምጣት ይችላሉ። እንዲሁም ልጅዎን ለማረጋጋት እንዲረዳው ፓስፋየር፣ ብርድ ልብስ፣ ወይም የሚወደው አሻንጉሊት ይዘው ይምጡ።

ልጅዎን ዚፐሮች እና መቆንጠጫዎች የሌለው የምቾት ልብስ ያልብሱት። ፉልፎ አይነት ለስላሳ ልብሶች መልበስ ጥሩ ምርጫ ነው።

ስካን በሚደረግበት ጊዜ፡ ልጅዎ ሊመለከቷቸው የሚችል ቪዲዮዎች አሉን፤ ወይም ለመመልከት የሚወዱትን ቪዲዮ ወይም ዲቪዲ ካልዎት ከቤት ይዘው መምጣት ይችላሉ።

ስካን በሚደረግበት ቀን ልጅዎ ካፌይን የያዙ ፈሳሾችን (ለስላሳ መጠጦች፣ ሻይ፣ ቡና፣ ወዘተ የመሳሰሉት) መጠጣት የለበትም።



### የበለጠ ለማወቅ

- ራዲዮሎጂ
  206-987-2089
- የልጅዎን ነርስ ወይም የጤና እንክብካቤ አቅራቢን ይጠይቁ።
- seattlechildrens.org

### ነጻ የአስተርጓሚ አገልግሎቶች

- በሆስፒታል ውስጥ ነርስዎን ይጠይቁ።
- ከሆስፒታሉ ውጭ በነጻ የሚያገለግል የቤተሰብ አስተርጓሚ መስመርን፡ በ 1-866-583-1527 ይደውሉ። የሚፈልጉትን ስም ወይም ኤክስተንሽን ለአስተርጓሚው ያስታውቁ።

Seattle Children's®
HOSPITAL • RESEARCH • FOUNDATION

**ለቀጠሮው እንዴት ተመዝግበን እንገባለን?**

ከተያዘለት ቀጠሮ 20 ደቂቃዎች አስቀድመው ይድረሱ። አርፍዶ መምጣት ሌሎች ቀጠሮዎችን ሊነካ ስለሚችል፡ የእርስዎ  ቀጠሮዎን ሊያዘገይ ይችላል። የሚዘገዩ ከሆነ፡ እባክዎን ወደ ራዲዮሎጂ በስ.ቁ 206-987-2089 ይደውሉ።

በ Ocean መግቢያ ወደ ውስጥ ሲገቡ ያለው ደረጃ 6 የምዝገባ ጠረጴዛ ላይ ተመዝግበው ይግቡ። ምዝገባውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደ ራዲዮሎጂ መቀበያ ቦታ እንዲሄዱ ይደረጋል።

**በኩላሊት የስካን ምርመራ ጊዜ ምን ይሆናል?**

ነርስ የመከታተል ጠቋሚው መርፌ ወደ ልጅዎ የደም ስር IV (ትንሽ መርፌ በደም ሥር) ያስገባል። ልጅዎ ልክ እንደ ትንሽ የመቆንጠጥ ስሜት ብቻ ነው የሚሰማው። ልጅዎ በመቃኛ አልጋ ላይ ይተኛል፡ እና ከታች ባለው ልዩ ካሜራ ፎቶ ይነሳል። ይህ የፎቶ ክፍለ ጊዜ ለ60 ደቂቃዎች ያህል ይቆያል። ስካኑ እየተካሄደ በመሀል 15 ደቂቃ በኋላ ልጅዎ ለይዚክስ (diuretic) የሚባል መድሃኒት ሊሰጠው ይችላል። ሌይሲኩ በ IV በኩል ይሰጣል እንዲሁም በልጅዎ ላይ ምንም የጎንዮሽ ጉዳት አይኖረውም።

IV በሚሰጥበት ጊዜ እና ፎቶዎቹ በሚነሱበት ጊዜ ልጅዎ መንቀሳቀስ የለበትም። በእነዚህ ጊዜያት ልጆች ሳይንቀሳቀሱ መቆየት አብዛኛውን ጊዜ በጣም ከባድ ነው የሚሆነው። ልጅዎ አሁንም ሳይንቀሳቀስ መቆየት ካልቻለ፡ ሰራተኞቻችን ልጁ እንዳይቀሳቀስ በመያዝ ረገድ ይረዷቸዋል።

በጠቅላላው የስካን ጊዜ ወላጆች ከልጃቸው ጋር ሊቆዩ ይችላሉ። እባክዎን ለወንድማማቾችና እኅትማማቾች ሌላ ዝግጅት አድርጉ።

**ለይዚክስ የኩላሊት ስካን ጨረር ይጠቀማል?**

አዎን፡ ልጅዎ ለትንሽ ጨረር ይጋለጣል። የጨረር መጠን ለልጆች አሳሳቢ ጉዳይ እንደሆነ ይገባናል። ልጅዎ የሚጋለጥበት የጨረር መጠን ለመቀነስ፡ በልጅዎ ዕድሜ፣ ክብደት እና የሚመረመርበት የአካል ክፍል ላይ መሰረት በማድረግ የሌይሲክ የኩላሊት ስካን ምርመራውን እናዘጋጃለን።

ስለ ምርመራው እንዲሁም ምርመራው አስፈላጊ ስለመሆኑ ጥያቄዎች ካሉዎት፡ እባክዎን ለልጅዎ ስካን ያዘዘውን ዶክተር ያነጋግሩ።

**ስካን ከተደረገ በኋላ ምን ይሆናል?**

የስካን ምርመራው ሲጠናቀቅ የቴክኖሎጂ ባለሙያው ያሳውቅዎታል። IV ይወጣል እና ልጅዎ ወደ መደበኛ የእለት ተእለት እንቅስቃሴዎች ሊመለስ ይችላል።

ልጅዎ በሚሸናበት ጊዜ መከታተያ ጠቋሚውን ከሰውነቱ ያስወግዳል።

ከብዙ ሰዓታት በኋላ ከልጅዎ ሰውነት ውስጥ ሙሉ በሙሉ መውጣት አለበት።

በልጅዎ የራዲዮሎጂ ሂደት ውስጥ የተነሱ ስእሎች በተለምዶ በ 24 ሰዓታት ውስጥ በራዲዮሎጂስት ይገመገማሉ፡ እና ሪፖርቱ ምርመራውን ወደ ያዘዘው ዶክተር ይላካል። የክሊኒክ ወይም የዶክተር ቀጠሮ ካለዎት ሐኪሙ በቀጠሮው ቀን ላይ ስለ ውጤቱ ከእርስዎ ጋር ይነጋገራል። ቀጠሮ ከሌለዎት የምርመራው ውጤቱን ለማግኘት የልጅዎን ከሐኪሙ ጋር ለመነጋገር መደወል  አለብዎት።

Seattle Children's መስማት ለተሳናቸው፣ የመስማት ችግር ላለባቸው ወይም የእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር ለማይችሉ ህመምተኞች፣ ለቤተሰብ አባላት፣ እና ለህጋዊ ተወካዮች የአስተርጓሚ አገልግሎቶችን በነጻ ይሰጣል። የ Seattle Children's በተጠየቁ ጊዜ ይህንን መረጃ እንደ አማራጭ በሌላ ቅርጸቶች ያቀርባል። በ 206-987-2201 ለ Family Resource Center ይደውሉ። ይህ የሚታደል ጽሑፍ በ Seattle Children's ክሊኒካዊ ሠራተኞች ተገምግሟል። ቢሆንም፡ የልጅዎ ፍላጎቶች ከሌሎች ልጆች ፍላጎት የተለዩ ናቸው። በዚህ መረጃ ላይ እርምጃ ከመውሰድዎ ወይም ከመተማመንዎ በፊት፡ እባክዎ ከልጅዎ የጤና አጠባበቅ አቅራቢ ጋር ይነጋገሩ።

© 2020 Seattle Children's፡ ሲያትል፡ ዋሽንግተን። መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

6/20
PE677AM

# Lasix Renal Scan



## What is a Lasix renal scan?

A Lasix renal scan is a test that shows how well your child's kidneys are working and if there is anything blocking the kidneys, ureters and bladder (urinary system). The test is also called a MAG-3 renogram. We will inject a small amount of a tracer (radiopharmaceutical) into your child's veins. Once the tracer is in your child's body, we take pictures of the urinary system. After the scan, we will do a measurement to compare the amount of kidney function in the right and left kidneys.

## How do I prepare my child for the scan?

Explain what will happen during the scan to your child before you come to the hospital.

If your child is a baby, you may want to bring a bottle of formula or juice with you for after the scan. Also, consider bringing a pacifier, blanket or special toy to help calm your child.

Dress your child comfortably in clothes without zippers or snaps. Sweats are a good choice.

We have videos your child can watch, or they can bring their favorite video or DVD from home to watch during the scan.

Your child should not drink fluids that contain caffeine (soft drinks, tea, coffee, etc.) on the day of the scan.

## How do we check in for the appointment?

Arrive 20 minutes before your scheduled appointment. Being late can affect other appointments and can delay your appointment. If you will be late, please call Radiology at 206-987-2089.

Check in at the level 6 registration desk inside the Ocean entrance. After you complete registration, you will be directed to the Radiology reception area.

## What happens during a renal scan?

A nurse will place an IV (small needle in the vein) in your child for the tracer injection. Your child will only feel a little discomfort, like a mild pinch. Your child will lie on a scanning bed while pictures are taken with a special camera that is located below them. This picture session lasts about 60 minutes. Your child may be given a medicine called Lasix (a diuretic) about 15 minutes into the scan. The Lasix is given through the IV and will have no side effects on your child.

Your child will need to be still while the IV is placed and while the pictures are taken. It is often difficult for children to lie still during these times. If your child is unable to lie still, our staff will assist them in holding still.

Parents may stay with their child during the entire scan. Please make other arrangements for siblings.

## Does the Lasix renal scan use radiation?

Yes, your child will be exposed to a small amount of radiation. We understand that radiation dose is a special concern for children. To minimize how much radiation your child is exposed to, we customize the Lasix renal scan based on your child's age, weight and area to be examined.

If you have questions about the exam and whether it is needed, please contact the doctor who ordered the scan for your child.

## What happens after the scan?

The technologist will tell you when the scan is complete. The IV will be removed and your child may return to normal daily activities.

Your child will remove the tracer from their body when they pee.

It should be completely out of your child's body within several hours.

The images from your child's radiology procedure are typically reviewed by a radiologist within 24 hours, and a report will be sent to the doctor who ordered the test. If you have a clinic or doctor appointment scheduled, the doctor will review the results with you then. If you do not have a visit scheduled, you should call your child's doctor for the results.

Seattle Children's offers interpreter services for Deaf, hard of hearing or non-English speaking patients, family members and legal representatives free of charge. Seattle Children's will make this information available in alternate formats upon request. Call the Family Resource Center at 206-987-2201. This handout has been reviewed by clinical staff at Seattle Children's. However, your child's needs are unique. Before you act or rely upon this information, please talk with your child's healthcare provider.

© 2020 Seattle Children's, Seattle, Washington. All rights reserved.

6/20
PE677